## ***የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤***
## ***<u>ከዚኽ ወዴት</u>?***

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

### ***<u>ክፍል ሁለት ( ከክፍል አንድ የቀጠለ)</u>***

### **<u>ለ) ሕወሓት/ኢሕአዴግ፤</u>**

*አገራችን እንደ አገር መንግሥታዊ ሥርዓት ካቆመችበት ከንጉሥ ሰብታኅ (ከ ፪ ሽህ ፭፻፵፭ ዓመተ-ዓለም – 2,545 BC) ጀምሮ የቆየውን ዘውዳዊ ሥርዓት በማስወገድ ለአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትኅን፣ እኩልነትንና የመብት ባለቤትነትን ለማጎናጠፍ በኅውን በማሰብ ኅማን፣ ቋንቋን ሐይማኖትን፣ ፆታን፣ አካባቢን፣ ዕድሜን፣ ሙያን፣ ወዘተ.. ሳይለይ ከዳር--እስከ-ዳር በአንዲት አገር ዜጋ መንፈስ የተነሣውና በጅምላው “የተማሪው እንቅስቃሴ” በመባል የሚታወቀው ነውጥ በውስጡ ልዩ ልዩ አዝማሚያዎችን የሚያቀነቅኑና ለተለያዩ ግቦች የቆሙ ኃይሎችን አቅፎ የያዘ እንደነበር ግልፅ ነው። በጥቅሉ “ተራማጅ” ከተባለው ይኽ ክፍል ውስጥ ከነበሩ ዋና ዋና የኃይል አሰላለፎች መኻል ሁለት ነጥረውና ጎልተው የወጡ አዝማሚያዎች ነበሩ። እነዚኽም በአንድ በኩል ኅብረተሰቡን በመደብ በከተረ-መልኩ ለብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትኅንና እኩልነትን የሚያጎናጥፍና የመብቶቹ ባለቤት የሚያደርግ ሥርዓት ከማስገኘት ውጭ የኢትዮጵያን በአንድ አገር የመቀጠል ጉዳይ ምንም ጥያቄ ውስጥ ያላስገባው “ተራማጅ የአንድነት” ወገን ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአገሪቱ ያለው “ዋናው ቅራኔ የብሔር/ብሔረ-ሰቦች ነው፣ ኢትዮጵያ የብሔር/ብሔረ-ሰቦች እስር ቤት ናት፣ ስለሆነም እያንዳንዱ የየራሱን መንግሥት መመሥረት አለበት፣ ወዘተ..” በሚል ፍልሥፍና የተሰለፈውና በዚኽ መርኅ የተደራጀው “የኅጥ/የኅሣ ብሔረሰበኛ” ክፍል ነበር። በእርግጥ “ተራማጅ የአንድነት” ከተባለው ክፍል ከሞላ-ጎደል ሁሉም ማለት በሚቻልበት ደረጃ ይኽንን “የብሔር/ብሔረ-ሰቦች” ጥያቄ “የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል” የሚል ጥቅል አቋም የያዘበት (“የተቀበለበት”) እና ያን ዓይነት ደፈናዊ አቋም መውሰድም “የተራማጅነት” አንደኛው ዘይቤ ተደርጎ ይታይ እንደነበር ይታወቃል።*

*በሁሉም የፖለቲካ አዝማሚያዎች የተሰለፉት እኒኽ በኅ ራዕይ-አንጋቢ ወጣት የአገሪቱ ዜጎች አፍላ ጉልበታቸውና ለጋ ዕድሜአቸው በፈቀደላቸው መጠን ለግል ዝናና ጥቅም ሣይሆን ለየቆሙበት ዓላማ እራሣቸውን አሣልፈው ለመስጠት የቆረጡ መሆናቸውን በከፈሉት መጠነ-ሠፊ መስዋዕትነት በተግባር አስመስክረዋል። በዚኽ ለተሻለ ተስፋ በተደረገ ሰልፍና ፍልሚያም ትምሕርት ቤት የገባው ብቻ ሣይሆን ለመማር አቅምም ሆነ ዕድል ያልነበረው ገጠሬና ከተሜ መስዋዕት በመሆኑ ረገድ ለለውጥ ያለውን ጉጉት፣ ቀና መንፈስና ዝግጁነት እኩል አሣይቷል፤ የዜግነት ድርሻውንም ተወጥቷል።*
*ከዚኽ በዋናነት በተማሪው ክፍል ከተደረገው የተደራጀ አብዮታዊ ነውጥ በፊት በተለያዩ ጊዜዎችና ደረጃዎች ለአገረ-ኢትዮጵያና ለሕዝቧ አጠቃላይ መብት፣ እድገትና ብልጽግናም ይሁን አካባቢ-ተኮር ጥያቄን በማንሣት በግልም ሆነ በቡድን ደረጃ የተደረጉ ጥረቶችና እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ደግሞ ሊዘነጋ አይገባም።*

*“በተማሪው እንቅስቃሴ” ወቅት በሁለቱም በኩል የተሰለፉት ኃይሎች የተለያዩ የመታገያ ስልቶችን መርጠው ለየቆሙበት ዓላማ በተለያዩ ዘዴዎችና ስልቶች ማለትም፤ መሠረቱን በገጠር ባደረገ ትጥቅ ትግል፣ የነበረውን ሥርዓት ጠገግ በተከተለ የውስጥ ርዕዮታዊ ትግል፣ በገጠርም በከተማም ሁለቱንም በቀላቀለ የትጥቅ ትግል በማድረግ እንደየ-ምርጫና አቅማቸው ታግለዋል። ከዚኽ ለውጥ-አንጋቢ እንቅስቃሴ እየተሰነጠሩ ከወጡ የልዩ ልዩ አዝማሚያ አራማጅ ኃይሎች መኻል አንዱ “የብሔር/ብሔረሰብ” ጥያቄ አቀንቃኝና አካባቢያቸውን “ነፃ የማውጣት” ዓላማን እውን ለማድረግ የታጠቀ ትግል ካደረጉት ውስጥ ላለፉት ሁለት አሥርተ-ዓመታት ያኽል በኢትዮጵያ አገራዊ ሥልጣን ይዞ የሚገኘው በወቅቱ ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ (የትግራይ ሕዝብ ነፃ-አውጭ ግንባር) - ቆይቶ*

ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (TPLF) - የተሰኘው ድርጅት ነው:: ይኸ ድርጅት ከተነሣበት ትግራይን "ነፃ" የማውጣት ተልዕኮ አሁን ወደሚገኝበት አገራዊ መንግሥትነት እንዴት እንደበቃም ሆነ ስለድርጅቱ የፖለቲካ ፍልሥፍና፣ ያን ፍልሥፍና የተከተለ አደረጃጀት፣ አመራር፣ አሠራርና ይዞታ ቀደም ሲል "ወያኔ ማነው?"(Woyane Manew.pdf) በሚል ርዕስ ለማሣየት ስለተሞከረ ዳግም እዚኸ ላይ መጥቀሱ አስፈላጊ አይሆንም:: ዋናው ጉዳይ ይኸ ኃይል በአሁኑ ጊዜ በኢሕአዴግ ጭምብል መንግሥታዊ ሥልጣን ይዞ የሚገኝና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጉዳይ በመጥፎም ሆነ በመልካም ጎን ወሳኝ ከሆኑት ሁለት ዋነኛ ኃይሎች መካከል አንዱ ነውና በዚኸ ጽሑፍ ላይ ይኸን ድርጅት ለማየት የምሞክረው ከዚኸ አኳያ ይሆናል:: እንግዲህ ድርጅቱ ከያዘው ሥልጣንና በዚኸም ሥልጣኑ የአገረ-ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ዕጣ-ፈንታ በመወሰኑ ረገድ እያደረገ ያለውንና ሊያደርግ የሚችለውን ምናልባትም የሚገባውን የወሳኝነት ድርሻ በሚመለከት ስለሆነ የሚታየው፣ ለአገላለፅ እንዲመች ድርጅቱን የምጠራው በአብዛኛው በዋና ስሙ በሕወሓት ሣይሆን በመንግሥታዊ የሥልጣን ስሙ በኢሕአዴግ ይሆናል:: ዞሮ ዞሮ የዚኸ ገዥ ፓርቲ ዋናው ማዕከልና ሙሉ ሥልጣንን በሁሉም ረገድ በበላይነት ሙጭጭ አድርገው የያዙት ሕወሓትና አባላቱ መሆናቸው ቢታወቅም፣ የሌሎችን ሽፋን፣ ትብብርና ፈቃደኛነት ባያገኝ ኖሮ የያዘውን መጠሪያ ይዞ አገራዊ መንግሥት ብቻውን መያዝ እንደማይችል ሁሉ በጥፋቱ ለመጠየቅም ሆነ በጎ ነገር ካለም ለመመስገን ተባባሪዎች ሁሉ እኩል ተጠያቂና ባለቤት ሊሆኑ ስለሚገባም ጭምር ነው በአብዛኛው ኢሕአዴግ በሚል መጠሪያው መቀጠሉን የመረጥኩት::

ቅድመም ሆነ ድኅረ-የተማሪው እንቅስቃሴ የተደረገው ትግል በአብዛኛው አገር-ተኮር የሆነና እንደ አንድ ሕዝብ ለመብቶች መከበርና ለብልጽግና ነበር ማለት ቢቻልም፤ የፖለቲካ ብሔረሰበኝነት (ፖለቲካዊ ጎሠኝነት) ዋና የመደራጃ ዘይቤ ከመሆን አልፎ መደበኛ መንግሥታዊ የ"አስተዳደር" ማዋቀሪያና መመሪያ መሆን ከተጀመረ ጊዜ ወዲኸ ግን ትግሉ መልኩን እየቀየረ ታሪክን መሠረት ያደረገና እንደ አንዲት አገር ዜጋ ለወል ጥቅምና ለጋራ ተስፋ ከማሰቡ ይልቅ ቋንቋንና ጎሣን (ብሔረሰብን) ቅድሚያ በሰጠ የተናጠል አስተሣሰብ የተገራና አሰላለፉም ይኸንኑ ጠገግ በተከተለ በልዩነት ላይ ያተኮረና ሕዝብን በሚያቀራርብ ሣይሆን በሚከፋፍል መልክ እየሆነ በመምጣቱ በአዘቦቱ የውጭ ባዕድ ጥቃት ሲሰነዝር ብቻ ይነሣ የነበር ኢትዮጵያ እንደ አንድ አገርና ሕዝቧም እንደ አንድ ነፃ ሕዝብ የመቀጠልና ያለመቀጠልን ያኸል እጅግ ከባድና መሠረታዊ የኀልውና ጥያቄ በአገር-ወዳድና በዴሞክራሲያዊ ወገኖች መነሣቱም ሆነ በሕዝብም ዘንድ ስጋት ማሳደሩ አይቀሬ ሆኗል::

በብዙ ወገኖች በየጊዜው እንደተነገረው ሁሉ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በስሌትም ይሁን ባለማወቅ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የሕዝቧን መብቶች አጥብቀው የሚጋፉ አልፎም ተፃርረው የቆሙ ጉልህ ጉልህ ውሳኔዎችን ማድረጉና እርምጃዎችን መውሰዱ የታወቀ ነው:: ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ ወዲህ የተደረጉ አንዳንድ "የግንባታ" እንቅስቃሴዎችን ላይ ላዩን በመመልከትና አገዛዙም የሚሰጣቸውን 'ሁለትና ሁለት አሥር' ዓይነት ያልተዛመደ ቀመር በግልቡ በመቀበል አገር "እየበለፀገች" እንደሆነ፣ አልፎም ለዝንታለም የተቆራኘን አሳፋሪ ድህነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊወገድ እንደሚችል፣ ወዘተ የሚናገሩ አንዳንድ ወገኖች እንዳሉ ይታወቃል:: ልክ ነው በብዙ ረገድ እንቅስቃሴዎች አሉ:: መኖርም ይገባቸዋል:: ሌላው ቀርቶ አስከፊው የደርግ ሥርዓትም ቢሆን ኢሕአዴግ ያገኘው ዓይነት አንፃራዊ ሰላም ቢኖረውና ኤኮኖሚው የጦርነት ኤኮኖሚ ባይሆንበት ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎች ሊኖሩ እንደሚችል መገመቱ ከባድ አይሆንም:: ደግሞም ኢሕአዴግ አደረገ የተባለውን ወይም እያደረገ ያለውን ባያደርግ ጉዳቱ ለማን ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው:: ብልፅግናንና ዕድገትን፤ በተለይም አገራችንን የተጠናወታት አንገት አስደፊና አሣፋሪ ረሃብ እንዲወገድ የማይፈልግ ብቻ ሣይሆን ቅድሚያ የማይሰጥ ጤናማ ዜጋ አይኖርም:: መሠረታዊ ጥያቄው ግን ማን አደረገው ሣይሆን መሠረታዊ መብቶቹ ያልተከበሩለት ሕዝብ በውሳኔዎቹ ላይ ምን ያኸል ድምፅ አለው፤ በዚኸ "ግንባታ" ውስጥ ያለው ሚናስ ምንድነው፣ ከውጤቶቹስ ምን ያኸል ተጠቃሚ ነው? እና የመሣሰሉት ሊሆኑ ይገባል::

መቸም የአገዛዙ መሪዎች ወደዱም ጠሉም፣ ፈለጉም አልፈለጉ በጉጉትና በስስት የሚያዩትን ሥልጣን ለማቆየት ከማሰብም ይሁን ለጊዚያዊ ፖለቲካዊ ጥቅም ወይም በሌሎች ምክንያቶች ከሚወስዷቸው ውሳኔዎችና ከሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች የአገርን ብሔራዊ ጥቅምና የሕዝብን ሉዓላዊ መብቶች የሚጋፉና የሚጎዱ እንደመኖራቸው ሁሉ በተወሰነ ደረጃም ይሁን እንጂ ከነዚኽ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ውስጥ በሂደት ሕዝብንና አገርን ሊጠቅሙ የሚችሉና ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይል ወደ-ፊት ሊደረጉ ይገባል ለሚላቸው ዓበይት ትልሞች የማይናቁ አስተዋፅዖዎች ሊያደርጉ የሚችሉ መኖራቸው የግድ ነው:: ለምሳሌ ሕዝብን ለመሸንገልና ጊዚያዊ እፎይታን ለማግኘት ከሚመነጭ ጊዚያዊ ፖለቲካዊ ስሊትም ይሁን ጠቀሜታቸው በቀጥታ ለገዥው ክፍል አባላት እንዲሆን በጠባብ አስተሳሰብ ተመርተው በስግብግብነት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሳይቀር ከዓይነታዎቹ ተጠቃሚ “ባለቤቶች” አቅምና ዕድሜ ወይም ከኢሕአዴግ በሥልጣን የመቆየት ጊዜ ያለፈና ለአገርና ለሕዝብ ዕድገት አስተዋፅዖ የሚኖራቸው ክንዋኔዎችና ግኝቶች እንደሚኖሩ ግልፅ ነው:: ለምሳሌ እንደ ግድብ፣ የመገናኛ አውታሮች፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ገዥው ፓርቲ ኖረም አልኖረም አገልግሎታቸውና ጠቀሜታቸው በቀላሉ የሚገመት አይሆንም:: (*በተለይ በግድቦቹ ዙሪያ ሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ)::* ችግሩ ያለው አንድም እነኝኽ እቅዶች ሲወጡና በተለይም በአፈፃጸም ውሳኔዎች ላይ የሕዝቡ ተሳትፎና ይሁንታ መኖርን፣ ሁለተኛም እቅዶቹ “ለስሚ መጠሪያ ቁና ሰፋች” ዓይነትና ይስሙላዊ የይድረስ የይድረስ ተግባር እንዳይሆንና በሕዝብ ላይ ያላስፈላጊና ግብታዊ መፈናቀል እንዳያስከትል፣ የሕዝብን መፈናቀል የግድ የሚጠይቅ ሲሆን ደግሞ መልሶ የማቋቋምና በቂና አግብባዊ ካሣ እንዲያገኝ ማድረግን እና በአካባቢው የአየርና የተፈጥሮ ጠባይ ላይ የሚያስከትለው ከጥቅሙ ጉዳቱ እንዳይበልጥ በቂ ጥናት ላይ እንዲመሠረት ማድረግን የሚጠይቁ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ እነዚኽ እጅግ አስፈላጊ ጉዳዮች በኢሕአዴግ ሲፈፀሙ አለመታየታቸው ላይ ነው:: አልፎም በ“ልማት” ስም ነገ የሚባል ነገር እንደሌለ በሚያስመስል ደረጃ የአገርንና የሕዝብን ንብረቶች በአሳዛኝ ሁኔታ ችብቸባውን ኃላፊነት በጎደለው መልክ እያጣደፉት መሆኑ በውል ተጠያቂነት የሌለው ዝርፊያ ከመሆን ውጭ ከአገር ልማት ጋር ያለው ዝምድና ምን እንደሆነ ለኔ ግልፅ አይደለም:: እንደዚኽ የመሣሰሉ ኃላፊነት የጎደላቸው ፍርደ-ገምድልና ዕብሪታዊ ውሳኔዎች ጉዳታቸው አሁን በሕዝብ ላይ በሚያደርሱት በደል ላይ የሚቆም ሣይሆን ውሳኔዎቹ ግብታዊ፣ አድሎዓዊና አብዛኛውን ሕዝብ ለድህነት፣ ድሃዉን ይበልጥ ያጣ-የነጣ ድሃ የሚያደርግና በአንፃሩ በጣም “ምርጥ” የሆኑ ጥቂቶችን ብቻ ቅጥ-ላጣ ሃብት የሚዳርግ በመሆኑ ውሎ-አድሮ ለብጥብጥና ለኅብረተሰብ ቀውስ በር ከፋች ነውና እጅግ አሳሳቢ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል::

ይኽ ገዥ ድርጅት የሚከተላቸው ጣምራ የፖለቲካ ፍልሥፍናዎች፣ ማለትም ዓብዮታዊ ዴሞክራሲ እና ፖለቲካዊ ጎሠኝነት ኅብረተሰብን ወደ መድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ሆነ ወደ አስተማማኝ፣ ቀጣይነት ያለውና የአገሪቱን ዜጎች በእኩል ተጠቃሚ ወደሚያደርግ የምጣኔ-ሃብት (የኤኮኖሚ) እንቅስቃሴ፣ ልማትና እድገት ሊወስድ ይሳነዋል:: ድኅረ-ምርጫ-የለሹ-ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ያለው ኢሕአዴግ የፖለቲካ ይዞታውንና መሠረታዊ ፍልሥፍናውን ሳይለቅ የአገዛዝ ዘይቤውን መለወጥ እንደሚኖርበት ግን የግድ ነው:: የዚኽ ምርጫ-ሁለት-ሽህ-ሁለት ሂደትና ውጤት ወሳኙ በአብዛኛው ታሪካዊው ምርጫ ዘጠና-ሰባት እንደሆነ አምናለሁ:: ያ 'ዳግም አድዋ' ሊሰኝ የሚችል መሰል-የለሽ ምርጫ በሕወሓት መሪዎች ላይ ያደረሰው ከባድ ሥነ-ልቦናዊ ምት ቀላል አልነበረም:: እንደኔ ለነ አቶ መለስ ምርጫ ዘጠና-ሰባት ማለት የባድሜ ጦርነት በነ አቶ ኢሣኢያስ ላይ ያደረሰው ወይም ዓድዋ በጣልያኖች ላይ ያስከተለው አእምሮ አቃዋሽና ውስጣዊ የማይሽር አሸማቃቂ፣ እንቅልፍ-ነሽና አብናኝ፣ የውርደት-ውርደት አከናናቢ ድርጊት ሊሆን እንደሚችል ነው:: ያ ዓይነት ሽንፈት ደግሞ ተራ ሽንፈት ሣይሆን በተቸናፊዎቹ ላይ ግላዊ የሆነ ከፍተኛ የመዋረድ ስሜትን የሚያሳድር፣ ምሬትና ቁጭት ውስጥ የሚጥልና በቀላሉ የማይሽር ከባድ የኅሊና ጠባሳ የሚተው መዘዝ አለው:: በመሆኑም ሽንፈቱ የወደፊቱን ብቻ ሣይሆን አለን የሚሉትን የቆየ እራስን አጉል አጋኖ ከማየት የመነጨ “ማን ሲደፍረኝ፣ አልበገርም” የሚል ግብዝ ትዕቢትን ጨርሶ ደምሳሽና አስተንፋሽ ድርጊት ነው:: ይኽ ውሳጣዊ ውርደት-ወለድ

ስሜት የለየለት፣ በንዴት የሚያቃጥልና ብርክ-አስያዥ ስለሆነ፣ ተረችዎቹ ሽንፈቱን በፀጋ መቀበል የሞት-ሞት አድርገው ስለሚቆጥሩት "ስምን ለማደስ" በውስጡ ብቀላን ባረገዘና ቂምን ባዘለ የተቃጠለ መንፈስ ምንም ዓይነት ውሳኔ ማድረግንና ማንኛውንም እርምጃ መውሰድን እንደ-ግል መለኮታዊ ተልዕኮ አድርገው ይቆጥሩታል:: እርምጃቸውም ቢያንስ ያ ሽንፈት ተመልሶ እንዳይደገም በተቻላቸው መጠን "ትምሕርት-ሰጭ" እንዲሆን ይፈልጋሉ:: የጣልያኖች አርባ ዓመት የፈጀ ዝግጅትና በኢትዮጵያ ላይ የፈፀሙት አረመኔዓዊ ዳግም ወረራ ሥሩ አድዋ ላይ የደረሰባቸው ውርደት-ወለድ ሃፍረት እንደሆነ ሁሉ የኢሣኢያስ አፈወርቂ ነገ እራሱን በሚለበልብ ተግባር በመሠማራት አክራሪ ክፍሎችን እስከ መደገፍ ጭምር መድረሱና የአፍሪቃ ቀንድን የመበጥበጥ ተልዕኮም ሰበቡ እራሱ በዕብሪት በቆሰቆሰው የባድመ ጦርነት ሳቢያ ምንም ማረጋገጫ ያልነበረው ሸዓብያዊ አጉል "አይበገሬነትና አይደፈሬ" ሥነ-ልቦናዊ ትምክኅቱ በመንኮታኮቱ እንደሆነ ግልፅ ነው:: እንዲሁም የነመለስ ዜናዊ የምርጫ-ሁለት-ሽህ-ሁለት ውጤት ምርጫ ዘጠና-ሰባት ያደረሰባቸው ሥነ-ልቦናዊ ኪሣራና ያም ውስጣዊ ነውጥ የፈጠረው ስሜት በምንም ዓይነት ግንቦት እንዳትደገም በቁርጠኝነት በተወሰደ ዙሪያ-ጥምጥም ዘመቻ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል:: ያም በመሆኑ ከአሁን በኋላ ይኸ ገዥ ፓርቲና መሪዎቹ የፖለቲካ አቋማቸውና የሚከተሏቸው መርኃ-እቅዶት (ፖሊሲዎች) ወደ-ቅድመ ዘጠና-ሰባት የሚመለከቱ አይሆኑም:: እንዲያውም እስከ ምርጫ-የለሹ ምርጫ-ሁለት-ሽህ-ሁለት ወደ-ነበረው የሰለለ የፖለቲካ "ክፍተት" ዞር ብሎ የማያይ እንደሚሆን ሊታወቅ ይገባል:: ስለሆነም የኢሕአዴግ መሪዎች ወለም-ዘለም በሌለበት ሁኔታ በኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ ሥርዓትን እያደላደሉ ነው:: ለዚኸም እውነታ በማስረጃነት እንደ ጃፓንና ስዊደን የመሣሰሉትን አገሮች መጠቃቀሳቸው እየተሰማ ነው:: መቸም ነገሩ "ዱባና ቅል" ነው:: ታሪክንም ሆነ በነዚኸ አገሮች በተቃዋሚነት የቆሙ ድርጅቶችን ሚና፣ ሕዝብ ያሉትን ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ የሲቪል ማኀበረሰቡና የዴሞክራሲ ተቋማት የሚገኙበትን ደረጃና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና ምን እንደሆነ ያላገናዘበ መንጠራራት ነው:: ካድሬዎቻቸውም ከዚኸ "የቀጥሉበት" ምልክት ተነስተው - እንዲያውም አለፍ ብለው - ምንም ሳያፍሩ ከአሁን በኋላ ኢሕአዴግ የአገሪቱ "አውራ ፓርቲ" ነው እያሉን ነው:: አውራ ካለ ጭፍራ መኖሩ የግድ ነውና ያ ማለት ደግሞ ከዚኸ በኋላ በአገሪቱ ፖለቲካ "ሕጋዊ" ተሣትፎ ለማድረግ "ድፍረቱ" ያላቸው ካሉ በግልፅ ለጭፍራ ሚናቸው "ሕጋዊ" ፈቃድ ያገኛሉ ማለት ነው:: መቸም "አምና የሞተውን አዬዋ ይለዋል" እንዲሉ ሆነና አሁንም በአገሪቱ "የመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት" እየተካሄደ ነው ሊሉን የሚቃጣቸው አይጠፉም:: "ሲሰማ የሞተን እያየ ቅበረው" እንደሚለው የአበው ብኂል ካልሆነ በስተቀር ከእንግዲኸ የሚደረገው ትግል ከዚኸ አኳያ የተቃኘና ምላሹም መጣኝ መሆን እንደሚኖርበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይና በተለይም ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይል በተገቢ ሊረዱት ይገባል:: ከአምስት ዓመታት በፊት ኢሕአዴግ ድኅረ-ምርጫ-ዘጠኛ-ሰባት ያደረገውና ለማድረግ ቆርጦ የተነሳው ተራ የድምፅ ሰረቃ ተደርጎ በቀላሉ እንዳይወሰድ በተለይ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ሲወተውት የነበረውም ለዚኸ ነበር:: በዚኸ "ሕወሓት/ኢሕአዴግ" በሚል ርዕስ የተጀመረውን ዳሰሣ ለጊዜው እዚኸ ላይ በመግታት በቀጣዩ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመውን የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይል ካየን በኋላ በሠፊው እመለስበታለሁ::

ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው የአንድነት ኃይል እስካሁን የተጓዘበትም ሆነ አሁን እየኳተነ የሚገኝበት አቋም፣ ይዞታና የኃይል አሠላለፍ ከዚኸ ወደ-ፊት ላለው ትግል አይሠራም:: ለምን እንደማይሠራና ምን መደረግ እንደሚያስፈልግ በቀጣዮቹ ጽሑፎች ለማሳየት እሞክራለሁ:: በአጭሩ ግን ሕዝባዊ ትግሉ መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ የተመሠረተ አዲስ ቅኝትና የኃይል አሰላለፍን ይጠይቃል:: ከዚኸ አኳያ በአገራችን ለውጥ እንዲኖር ከፈለግን እስካሁን ከተጓዝንበት መንገድና ይዘነው ከቆየነው መሥመር ትምሕርት ቀስመን በአዲስ መልክና በኢትዮጵያዊ መንፈስ ለመነሣት መዘጋጀት ያስፈልጋል:: ዝርዝሩን እናያለን::

***በክፍል ሦስት ይቀጥላል.......***